# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የባርቢኪው ፕሮግራም

የቤተ ክርስቲናችንን 7ኛ የምስረታ አመት ምክንያት በማድረግ ዛሬ ከፕሮግራም በኋላ በFoster Beach እናደርጋለን። ሁላችንም የበረከቱ ተካፋዮች እንድንሆን ተጋብዘናል።

### የገንዘብ ማሰባሰቢያ ቅጽ

ለሕንጻ ግዢ የገንዘብ ማሰባሰቢያ የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልታችሁ ያልመለሳችሁ ወገኖች እባካችሁ ሞልታችሁ ለዲያቆናት ስጡልን። የህንጻ ኮሚቴ አስተባባሪዎች። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

### የሚሽን አገልግሎት የጋራ አምልኮ

የዛሬ ሳምንት (Sep. 17) ልዩ የሚሽን አገልግሎት የአምልኮ ጊዜ ከሬቨንስውድ ባብቲስት ቤተ ክርስቲያን ጋር ይኖረናል። አላማው ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት በመተባበር በኢትዮጲያ የሚሰራ ሚሽነረን በመደገፍ የወንጌል አገልግሎት ለማካሄድ ነው። በእለቱ አብረን አናመልካለን፤ ለሚሽን ስራ የሚሆን ልዩ ስጦታ እንሰበስባለን፤ እንዲሁም ከፕሮግራም በኋላ እራት አብረን እንቆርሳለን። ለዚህ ፕሮግራም እየጸለይን እንድንቆይ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች።



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

ሽማግሌዎችን ለማግኘት:-
773-886-0818 (ሲሳይ)
773-865-6102 (ብረሃኑ)
773-507-0194 (ጋሽ አያሌው)
773-910-0485 (ፒተር)
773-961-5332 (ጌቱ)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

| | | |
|---|---|---|
| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2:10




እንኳን ለሰባተኛ አመት በአላችን አደረሳችሁ! እንኳን ለኢትዮጵያ አዲስ አመት ዋዜማ አደረሳችሁ!

**አቤንኤዘር!**

| | |
|---|---|
| Chicago Yemsrach Evangelical Church<br>4455 N. Seeley Avenue<br>Chicago, IL 60625 | መደበኛ ፕሮግራሞች<br>እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.<br>አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m. |
| **September 10, 2017** | **ጳጉሜን 5፤ 2009 ዓ.ም.** |

# የእለቱ ፕሮግራም መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................. | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| አምልኮ....................... | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| ቃል ........................... | ወንድም ፍቅሩ ቴንሶ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

## የሳምንቱ ጥቅስ

"ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፥ ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ።"

(መዝ. 103፡2)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 6602 N. Damen Ave., Chicago IL 60626 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ማክሰኞ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ዴሌቦ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |
| ወ/ም መስፍን ጌታቸው | ዕሮብ | 4631 N. Beacon St., Chicago, IL 60640 |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

## አቤንኤዘር!

*"ሳሙኤልም አንድ ድንጋይ ወስዶ በምጽጳና በሼን መካከል አኖረው ስሙንም። እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል ሲል አቤንኤዘር ብሎ ጠራው።" (1 ሳሙ 7፡12)*

እንኳን ለቤተ ክርስቲናችን ሰባተኛ አመት በዓል ጌታ አደረሳችሁ። እንዱም እንኳን ለ2010 የኢትዮጵያ አዲስ አመት ዋዜማ ጌታ አደረሳችሁ። በ2010 ክረምት ላይ ጥቂት ወንድሞችና እሕቶች እሁድ እየተገናኙ መጸለይ ጀመሩ። በቤት የጸሎት ሕብረት የተጀመረው አገልግሎት ጌታ ባርኮት በመጀመሪያ ወደ ሕብረት በመቀጠልም ወደ ቤተ ክርስቲያን ደረጃ አደገ። ቤተ ክርስቲያናችን September 12 ቀን 2010 በሬቨንስውድ ባብቲስት ክርስቲያን ትምህርት ቤት በአንድ ክፍል ውስጥ ተጀመረች።

እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲናችን እና በሕይወታችን የሰራውን የማዳን ስራ፣ የመታደግ ስራ እንዘክርና እንመሰክር ዘንድ ይገባናል። ተፈውሰው ለምስጋና እንደጎደሉት ዘጠኙ ለምጻሞች ሳይሆን ለማመስገን እንደተመለሰው አንዱ እኛም ዛሬ ያሳለፍናቸውን ሳባት የምህረትና የበረከት አመታት እያሰብን እናመሰግናለን። እግዚአብሔር ውለታውን እንረሳ ዘንድ አይፈልግም። እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብጽ ምድር ሲያወጣው በዘመኑ ሁሉ የእርሱን ማዳን እያሰበ፣ ማዳኑን ለመጪው ትውልድ እየዘከረ የፋሲካን በዓል እንዲያደርግ አዘዘው። ስለዚህም ዛሬም እኛ መዝሙረኛው ዳዊት እንደዘመረው ነብሳችንን "ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፥ ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ" እያልን የእግዚአብሔርን ውለታ እያሰብንና እየቆጠርን ልናመሰግነው ይገባናል። (መዝ. 103፡2)

ባሳለፍናቸው ሰባት አመታት በጌታ ቸርነት ብዙ መልካም ነገሮች በመካከላችን ሆነዋል። የቤተ ክርስቲያንችን መዋቅር ተጠናክሯል፤ አገልግሎቶች በዝተውልናል፤ የቅዱሳን ሕብረት አድጓል። ብዙ ጌታ የቀባቸው አገልጋዮች በመካከላችን ተገኝተው አስተምረውናል፤ መክረውናል። ትዝታ የተሞሉ የሕብረት ጊዜዎችን አሳልፈናል። ወገኖች ሲጠመቁ፣ በቅዱስ ጋብቻ ሲጣመሩ፣ ሕጻናት ለጌታ ሲሰጡ፣ ሰዎች ወደ ጌታ ሲመጡ አይተናል። ወንጌሉን ይዘን ወጥተን ማዳኑን መስክረናል። በጸሎት በፊቱ በመውደቅ ቃትተናል። ከሕጻናቶቻችን አንደበት የምስጋና ዜማ ሲወጣ፤ ቃሉ ሲነገር ሰምተናል። በዘመኑ ሚዲያ በመጠቀም የወንጌሉን ቃል በቅርብም በሩቅም ላሉ ሁሉ ለማድረስ ጥረናል። የምንወዳቸው ወገኖች በተለዩንም ጊዜ ጌታ አጽናንቶናል።

ዛሬ ጠንካራ የሆነ የሽማግሌዎች አመራር ቡድን አለን። በብዙ የወንድሞችና የአህዮች ሕብረት፣ በብዙ የሆድ ፍሬ፣ በብዙ የአገልግሎት ጸጋ ተባርከናል። እግዚአብሔር በቤተሰባዊ ህብረት፣ የቃሉን ደጅ በመክፈት፣ በክብሩ መገኘትና በመንፈሱ ልእልና ባርኮናል። ከሌሎች ቅዱሳን ጋር ያለንን ሕብረት በማደስና በማጠንከር ጌታ አዲስ ምዕራፍ ከፍቶልናል። በእርግጥም እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል፣ ደግሞም ይረዳናል። አቤንኤዘር!